# ኦሀናኤዜ ኢንዲኢቦ ኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅት

# (OHANAEZE NDIGBO ETHIOPIA CHARITY ORGANIZATION)

# መተዳደርያ ደንብ

ሰኔ /2015 ዓ.ም

**አንቀጽ 1፡ <u>መቋቋም</u>**

ኦሀናኤዜ ኢዲኢቦ ኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅት (OHANAEZE NDIGBO ETHIOPIA CHARITY በቀን 29/09/2015 **ዓ.ም** ተቋቁሟል፡፡

## አንቀጽ 2፡ <u>ስያሜ</u>

በዚህ መተዳደሪያ ደንብ የተቋቋመው ኦሀናኤዜ ኢዲኢቦ ኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅት (OHANAEZE NDIGBO ETHIOPIA CHARITY) ድርጅት የሚል ስም የሚጠራ ሲሆን ከዚህ በኋላ ድርጅት ተብሎ ይጠቀሳል፡፡

**አንቀጽ 3፡ <u>ዓላማ</u>**

ኦሀናኤዜ ኢዲኢቦ ኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅት ዓላማዎች

- ለችግር የተጋለጡ የህብረተሰብ ክፍሎች ኢኮኖሚያዊ ድጋፍ ማድረግ፤
- በጤና ተቋማት ላይ የሚታዩ የህክምና ቁሳቁሶች ችሮችን ለመቅረፍ የተለያዩ ግብአቶችን ማቅረብ፤
- ዝቅተኛ ገቢ ላላቸዉና ረዳትና ደጋፊ ለሌቸዉ አረጋውያን በቁሳቁስ ድጋፍ ማድረግ፤
- የትምህርት እድል ያላገኙ ወጣቶችን የትምህርት እድል እንዲያገኙ ማድረግ

**አንቀጽ 4፡ <u>የበጀት ዓመት</u>**

የበጎ አድራጎት የበጀት ዓመት <u>ሃምሌ 01</u> እስከ <u>ሰኔ 30</u> ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 5፡ <u>ትርጉም</u>**

1. ቦርድ ማለት በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ድርጅቱን ለመምራትና ለማስተዳደር በድርጅቱ መሥራች/መሥራቾች የሚሾም የበላይ አካል ነው፡፡
2. "ድርጅት" ማለት በዚህ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 1 ላይ ስሙ የተገለፀው ማህደር የበጎ አድራጎት ድርጅት ነው፡፡
3. "አዋጅ" ማለት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 1113/2011 ነው
4. "ባለሥልጣን" ማለት በአዋጅ ቁጥር 1113/2011 ንዑስ አንቀጽ 4 እና የፌደራል መንግስት የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣን ተግባር ለመወሰን ባወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 መሰረት የተቋቋመው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን ነው፡፡
5. ኦሀናኤዜ ኢዲኢቦ ኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅት (OHANAEZE NDIJBO ETHIOPIA CHARITY ማለት -------------- ነው፡፡

### አንቀጽ 6፡ መደበኛ አባላት

1. የሚከተሉትን መመዘኛዎች የሚያሟላ/የምታሟላ ማንኛውም/ዋም ኢትዮጵያዊ/ት ፤ ትውልደ ኢትዮጵየዊ እና የውጪ ዜጋ ሆኖ የመኖሪያ ፋቃድ ያለው/ያላት መደበኛ አባል መሆን ይችላል/ትችላለች፡፡
   - ሀ. የበጎ አድራጎት አላማና ግብ የሚያምን/ የምታምን፤
   - ለ. እድሜው/ዋ ከ18 ዓመት በላይ የሆነ/ች፣
   - ሐ. የበጎ አድራጎት የመተዳደሪያ ደንብ እንዲሁም በቦርድ በየጊዜው የሚወጡ የሥነ-ምግባር ደንቦችን የሚቀበል/የምትቀበልና ተግባራዊ የሚያደርግ/የምታደርግ፣
   - መ. በቦርድ አባላት በየጊዜው ስምምነት የሚደረግባቸውን ክፍያዎችና መዋጮዎች መክፈል የሚችል/የምትችል
   - ሠ. በህግ መብቱ/ቷ ያልተገፈፈ/ያልተገፈፈች፡፡
2. መስራች አባላትንና በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት የድርጅቱ ቦርድ ውሣኔ ተቀባይነት ያገኙ አባላትን ይይዛል፡፡

### አንቀጽ 7፡ የክብር አባላት

1. የበጎ አድራጎት አባል ያልሆኑና የበጎ አድራጎቱ አላማ ለማስፈጸም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከቱ፤ የድርጅቱ በሚሰራባቸው ዘርፎች ተሰማርተው ውጤታማና የለውጥ አርአያ በመሆን በጎ አድራጐት ድርጅት አባላት ከፍተኛ ተቀባይነትን ያገኙ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች በቦርድ ውሳኔ የክብር አባል ይሆናሉ፡፡
2. የክብር አባላት ድርጅቱ ውስጥ የመምረጥ የመመረጥና ድምፅ የመስጠት መብት አይኖራቸውም፡፡
3. የክብር አባላት በራስ ተነሳሽነት ካልሆነ በቀር የአባልነት መዋጮዎችንና ሌሎች ክፍያዎችን የመክፈል ግዴታ አይኖርባቸውም፡፡

### አንቀጽ 8፡ የአባላት መብት

1. ሁሉም መደበኛ አባላት እኩል መብት አላቸው:
2. የበጎ አድራጎት አባልነት ለወራሾችም ሆነ ለሌላ ሰው የማይተላለፍ የግል መብት ነው፡፡
3. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት መደበኛ አባል፡-
   - ሀ. የበጎ አድራጎት ዓላማና ተልእኮዎች መሳካት የሚጠቅሙ ማናቸውንም አይነት ስራዎች የመስራት፣
   - ለ. የመምረጥ፣ የመመረጥና ስለድርጅቱ እንቅስቃሴ ማንኛውንም መረጃ ጠይቆ የማግኘት፣
   - ሐ. በቦርድ ስብሰባ የመገኘት፣ ስለ ድረጅቱ እንቅስቃሴ አስተያየትና ድምጽ የመስጠት መብት አለው፡፡

**አንቀጽ 9፡ <u>የአባላት ግዴታ</u>**

1. ማንኛውም/ዋም አባል የአባልነት መዋጮን በወቅቱ የመክፈል ፣
2. አንድ አባል ከአባልነት ከመሰናበቱ/ቷ በፊት የሚፈለግበትን/የሚፈለግባትን ዕዳ የመክፈል
3. ማንኛውም አባል የበጎ አድራጐት ድርጅቱን የመተዳደሪያ ደንብ፣ በቦርድ የሚወጡ መመሪያዎችና ውሣኔዎችን የማክበር ፣
4. ማንኛውም አባል የበጎ አድራጎቱን አላማና የገባቸውን/የገባችውን ግዴታዎች የማክበር፣ የበጎ አድራጎቱን ንብረት የመንከባከብና የሚጠበቅበትን አገልግሎት የመስጠት ፣
5. **የበጎ አድራጎት** መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎች ላይ የመገኘት ግዴታ አለበት/አለባት:

**አንቀጽ 10፡ <u>የአባላት መዋጮና ሌሎች ክፍያዎች</u>**

1. የበጎ አድራጎት መዋጮና ሌሎች ክፍያዎች የሚደረጉበት ጊዜና መጠን በቦርድ ይወሰናል፡፡
2. ቦርዱ በሚወስነው የጊዜ ገደብ የማይከፍል/የማትከፍል ሰው በቦርዱ ውሳኔ መሰረት መቀጮ ይጣልበታል/ይጣልባታል፡፡
3. የአባልነት መዋጮ ባለመክፈሉ/ሏ ምክንያት በቦርዱ የተጣለበትን/የተጣለባትን ቅጣት ያልከፈለ/ች አባል ላይ እዳውን/እዳዋን እስኪከፍል/እስክትከፍል ድረስ በቦርድ ድምፅ የመስጠት ወይም ማንኛውንም ሌላ መብት ሊያነሳ ይችላል:

**አንቀጽ 11፡ <u>አባልነት ስለሚቋረጥባቸው ሁኔታዎች</u>**


አንድ የበጎ አድራጎት አባል አባልነቱ/ቷ የሚቋረጠው፡-

1. ሲሞት/ስትሞት፣
2. መተዳደሪያ ደንቡ ላይ በተገለጸው መሠረት ወይም በሌላ አጥጋቢ ምክንያት ከአባልነት እንዲሰናበት/እንድትሰናበት ቦርዱ ሲወስን፣
3. የበጎ አድራጎት ክብርና ህልውና በሚነካ ወይም በሚያናጋ ተግባር ላይ መሳተፉ/ፏ በማስረጃ ሲረጋገጥና ይህም ቦርዱ ሲወሰን፣
4. የበጎ አድራጎት ዓላማ መሣካት በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ተገቢውን ተሣትፎ ለማድረግ ፍቃደኛ ሳይሆን/ሳትሆን ሲቀር/ስትቀር እና ይኸው በቦርድ ሲወሰን፣
5. መዋጮውን ለአንድ አመት ያህል ጊዜ ባለመክፈሉ/ሏ በቦርዱ ከአባልነቱ/ቷ ሲሰናበት/ስትሰናበት፣

6. ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ችሎታው/ዋን ወይም መብቱን/ዋን ሲነጠቅ/ስትነጠቅ ወይም ከአባልነት ሲወገድ/ስትወገድ፣
7. የበጎ አድራጎት አባልነት በራሱ/ሷ ፈቃድ ለመልቀቅ በጽሁፍ ሲጠይቅ/ስትጠይቅ ይሆናል፣

**አንቀጽ 12 የድርጅቱ አደረጃጀት**

1. የበጎ አድራጎት ድርጅት ቦርድ፣ሥራ አስኪያጅ፣ኦዲተር፣ሂሳብሹም፣ገንዘብ ያዥና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች ይኖረዋል።
2. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ በሚከተለው መልኩ የተዋቀረ ነው: -
3. የቦርድ አባል የሆነ ማናቸውም ሰው በተጨማሪ ኦዲተር ወይም ሥራአስኪያጅ ሆኖ ሊሰራ አይችልም።




4. የቦርድ አባል የሆነ ማናቸውም ሰው በተጨማሪ ኦዲተርወይምሥራአስኪያጅ ሆኖ ሊሰራ አይችልም።

**አንቀጽ 13፡ የቦርድ ስልጣንና ተግባር**

1. ቦርዱ በዚህ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 6 ላይ የተጠቀሱትን መደበኛ አባላት የሚያካትት ሆኖ በህግና ድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ. ቦርዱ የድርጅቱ የበላይ አካል ነው፣

ለ. የበጎ አድራጎት መተዳደሪያ ደንብ ያሻሽላል

ሐ. በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት የድርጅቱ ኦዲተር ይመርጣል፣ ያስናብታል፣ክፍያውን ይወስናል፣

መ. የቦርድ አባላትን፣ የቦርድ ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ እና የበጎ አድራጎት ስራ አስኪያጅ ይሾማል ይሽራል፣

ሠ. የበጎ አድራጎት ዋና መስሪያ ቤት የመለወጥና ቅርንጫፎች የመክፈት የመጨረሻ ውሳኔ ያሳልፋል፣

ረ. የበጎ አድራጎት መፍረስና ንብረት ማጣራት ላይ ይወስናል፣

ሰ. ድርጅቱ ዓመታዊ የስራ ክንውን ሪፖርት፣ የሂሳብ መግለጫ፣ የኦዲት ሪፖርትና ዓመታዊ በጀት ያፀድቃል፣

ሸ. ዓመታዊ የስራ ፕሮግራምን በመመርመር እቅድና በጀት ያፀድቃል፣

ቀ. የበጎ አድራጎት የፖሊሲና የስትራቴጂ ጉዳዮች ላይ ይወስናል፣

በ. የበጎ አድራጎት አባል ለመሆን በቀረበው ጥያቄ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፣

ተ. በዚህ መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 9 በተገለፀው መሠረት ግዴታውን ያልተወጣ አባልን ጉዳይ መርምሮ ከአባልነት እንዲሰረዝ ይወስናል፣

ቸ. የአባላት መዋጮ ሌሎች ክፍያዎችንና የቅጣት መጠን ላይ ይወስናል፣

ኀ. የበጎ አድራጎት ሂሳብ በውጭ ኦዲተር እንዲመረመር ያደርጋል፣

ነ. የቦርዱን የስብሰባ ሥነ-ስርዓት ደንብ ያወጣል፣

ኘ. የበጎ አድራጎት ከሌሎች የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ጋር ህብረት ለመፍጠር ወይም ለመዋሃድ ወይም የመከፈል ወይም የመለወጥ የመጨረሻ ውጣኔ ይሠጣል።

አ. የበጎ አድራጎት ሌሎች አካላት ስልጣንና ተግባራት ስር በማይወድቁ በጎ አድራጎት በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ይወስናል:

ከ. በበጎ አድራጐት ድርጅት የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ዕቅድና በጀት ላይ በመምከር ያጸድቃል፣

ወ. የበጎ አድራጎት ድርጅት ሠራተኞች የሚቀጠሩበትንና የሚተዳደሩበትን ደንብ ያወጣል፣

ዐ. የሚሰጡ ውሣኔዎችንና የሚወጡ እቅዶችን በሥራ አስኪያጁ ተግባራዊ መደረጋቸውን ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፣

ዘ. በገንዘብ ወይም በማቴሪያል ለበጎ አድራጐት ድርጅቱ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚሆኑ ገቢዎች መኖራቸውን ያረጋግጣል፣ ድጋፍ የሚገኝበትንም መንገድ ይቀይሳል፣

ዠ. የበጎ አድራጐት ድርጅት የማኔጅመንት አካላት የሚቀርቡ የሥራ አፈፃፀም ሪፖርቶችን መርምሮ ያጸድቃል፣

የ. የበጎ አድራጎት ድርጅት ፖሊሲ ለማውጣት ወይም ለማሻሻል የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ሥራ አስፈፃሚ አካል የሚያቀርባቸውን ሀሳቦች ተቀብሎና አስፈላጊም ሲሆን የራሱን አስተያየት ጨምሮ ውሣኔ እንዲሰጥባቸው ለጉባኤው ያቀርባል፣

ደ. ቦርዱ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ህግጋት ጋር ግጭት ከሌለው በስተቀር በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ትርጉም ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል።

ጀ. የበጎ አድራጎት የባንክ ሂሳብ የሚያንቀሳቅሱ ፈራሚዎችን የበጎ አድራጎት ስራ አስኪያጅ እና ሂሳብ ሹም በተጨማሪ ከድርጅቱ ሰራተኞች ሊወስን ይችላል።

ጸ. የበጎ አድራጎት ከሀገር ውጪ ቅርንጫፍ በሚከፍትበት ወቅት የድርጅቱን ተወካይ ይሾማል።

**አንቀጽ 14:** <u>**የቦርድ ድምጽ አሰጣጥ**</u>

1. ማንኛውም አባል በቦርድ ስብሰባ ላይ ተገኝቶ/ታ ድምፅ በሚሰጥበት ጉዳይ ላይ የሚሰጠው/የምትሰጠው ድምጽ አንድ ብቻ ይሆናል:
2. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት አባላት እኩል ድምጽ አላቸው:
3. ቦርዱ በግልጽ ካልፈቀደ በስተቀር ማንኛውም አባል በስብሰባ ላይ እራሱ/ሷ ተገኝቶ/ታ ድምጽ መስጠት ይኖርበታል/ይኖርባታል:
4. የድምጽ አሰጣጡ ሥነ-ሥርዓት ፍትሀዊ ነፃና ግልጽ በሆነ መንገድ ተፈፃሚ ይሆናል:
5. ከቦርዱ የተለየ ሃሣብ ያለው/ያላት የበጎ አድራት ድርጅቱ አባል የልዩነት ሀሣቡን/ቧን በቃለ ጉባኤው ላይ ለይቶ ማስፈር ይችላል/ትችላለች:
6. ማንኛውም መደበኛ የድርጅቱ አባል በቦርዱ የተላለፈው ውሣኔ የሃገሪቱን ህግጋት ወይም የበጎ አድራት ድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ ይጥሳል ብሎ/ላ ሲያምን/ስታምን ለባለስልጣኑ ሊያመለክት/ልታመለክት ይችላል/ትችላለች:

**አንቀጽ 15** <u>**የቦርድ አመራር አካላት ስልጣንና ተግባራት**</u>

1. የሥራ አመራር ቦርድ ከ5-13 አባላት ይኖሩታል፣
2. ቦርዱ ሰብሳቢውንና ምክትል ሰብሳቢውን ፀሐፊውን ይመርጣል፣

የቦርዱ ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ እና ፀሐፊ ስልጣንና ተግባራቸውም የሚከተለው ነው፣

1. <u>የቦርዱ ሰብሳቢ፣</u>

ሀ. የቦርዱን ስብሰባዎች ይጠራል/ትጠራለች ከጸሀፊው/ዋ ጋር በመሆን አጀንዳዎችን ያዘጋጃል/ታዘጋጃለች፣

ለ. የጉባዔውን ስብሰባ በሊቀመንበርነት ይመራል/ትመራለች፣

ሐ. ቦርዱ የሚያወጣቸውን ደንቦችና የሚሰጣቸውን ውሣኔዎች በትክክል ስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል/ትከታተላለች፣

መ. ቦርዱ ያጸደቃቸው የሩብ ፣የግማሽ እና ዓመታዊ የሥራ ክንውን ሪፖርት እና እቅድ እንዲሁም አመታዊ የኦዲት ሪፖርቶችና የሂሳብ መግለጫ ለሚመለከታቸው መንግሥታዊ አካላት እና እንደአስፈላጊነቱ ለተጠቃሚዎችና ለለጋሾች እንዲደርሱ ያደርጋል/ታደርጋለች፣

ሠ. ለጉባኤው የሚቀርቡ ጉዳዮችን ቅደም ተከተል በማውጣት ለውይይት እንዲቀርቡ ለፀሐፊው/ዋ በአጀንዳነት ያስይዛል/ታስይዛለች፣

ረ. ተጠሪነቱ ለቦርዱ ይሆናል፣

ሰ. ቦርዱ የሚያሳልፏቸው ውሣኔዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ለሥራ አስኪያጁ ትዕዛዝ ያስተላልፋል፣

ሸ. የበጎ አድሪጎት ድረርጅቱ ማኔጅመንት የሥራ አፈፃፀም በቅርብ ይከታተላል፣

ቀ. ከኦዲት ሪፖርት ውጭ ያሉትን ዓመታዊ ሪፖርቶች በጉባኤው መደበኛ ስብሰባ ላይ ያቀርባል፡

2. <u>ምክትል ሰብሳቢ</u>

   ሀ. ሰበሳቢው/ዋ በማይኖርበት/በማትኖርበት ጊዜ ተክቶ/ታ ይሠራል/ትሰራለች፣

   ለ. በሰብሳቢው/ዋ ወይም ቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ስራዎች ያከናውናል/ታከናውናለች፣

3. <u>ፀሐፊ</u>

   ሀ. ከሰብሳቢው/ዋ ጋር በመሆን ለጉባኤው አጀንዳዎችን ያዘጋጃል/ታዘጋጃለች፣

   ለ. የጉባኤውን ስብሰባ ቃለ ጉብኤ ይይዛል/ትይዛለች፣

   መ. የቦርዱ ጽ/ቤት መዛግብትና ሠነድ ይጠብቃል፡፡

**አንቀጽ 16: <u>የቦርድ ስብሰባ</u>**

1. የቦርዱ መድበኛ ስብሰባ በዓመት አራት ጊዜ የሚከናወን ሆኖ አስቸኳይ ስብሰባ የሚያስፈልግበት ምክንያት ሲኖር ልዩ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፣
2. የበጎ አድራጎት አስቸኳይ ስብሰባ በማናቸውም ጊዜ በቦርዱ ሰብሳቢ ወይም ከቦርድ አባላት 10 ከመቶ የሚሆኑት በሚጠይቁበት ጊዜ ሊካሄድ ይችላል፡፡
3. ለቦርዱ መደበኛ ስብሰባ አስራ አምስት የስራ ቀናት ለአስቸኳይ ስብሰባ ደግሞ ከአምስት የስራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ በፊት አባላት የስብሰባው ዝርዝር ጉዳይ፣ ቦታውን፣ቀኑን፣ እንዲያውቁት ይደረጋል፡፡
4. የበጎ አድራጎት አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

5. በዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 4 የተደነገገው እንዳለ ሆኖ ምልዓተ ጉባኤው ለሁለት ተከታታይ ስብሰባዎች ካልተሟላ የቦርድ ሰብሳቢ የሚቀጥለው ስብሰባ በተገኙት አባላት እንዲካሄድ ያደርጋል/ታደርጋለች፡፡
6. የቦርድ መደበኛ ስብሰባ ላይ የተለያዩ ጉዳዮች እንደየሁኔታው በአጀንዳነት ተይዘው ለውይይት ይቀርባሉ፣ ማንኛውም ጉዳይ በአጀንዳነት እንዲያዝለት የሚፈልግ አባል ቦርዱ ከመሰብሰቡ ቢያንስ ከአንድ ሳምንት በፊት ለቦርዱ ሰብሳቢ/ምክትል ሰብሳቢ/ፀሐፊበጽሁፍ ይህንኑ ማስታወቅ ይኖርበታል/ይኖርባታል፡፡

አንቀጽ17: <u>የምርጫና የውሣኔ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት</u>

1. በጎ አድራጎት ድርጅቱ የሚመራው በአባላት ሙሉ ተሳትፎ በተመረጡ ሰዎች ይሆናል፣
2. ጉባኤው ምርጫ ሲያደርግ ምልዓተ ጉባኤው እንደተሟላ የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት ተመርጠው ምርጫው እንዲካሄድ ያደርጋሉ፣
3. አስመራጭ ኮሚቴው ከሁሉ አስቀድሞ የምርጫ መመዘኛዎች በጉባኤው እንዲወስኑ አድርጎ ምርጫውን ያስፈጽማል፣
4. ቦርዱ የአገልግሎት ዘመናቸውን ያጠናቀቁ ወይም የተሻሩ ወይም በተለያዩ ምክንያቶች የተጓደሉ የቦርድ አመራር አባላትን ለመተካት እንደአስፈላጊነቱ የአስመራጭ ኮሚቴ ያቋቁማል፣
5. የምርጫ ዘመናቸውን ያጠናቀቁ ተመራጮች በድጋሚ እንዲያገለግሉ ከተፈለገ በጥቆማ ለውድድር ቀርበው በድምጽ ብልጫ መመረጥ ይኖርባቸዋል፣ ሆኖም ለ3ኛ ጊዜ ለመመረጥ ቢያንስ ለአንድ የምርጫ ዘመን ማረፍ ይኖርባቸዋል፡፡
6. የቦርዱ ውሳኔዎች በድምፅ ብልጫ ያልፋሉ፣ ድምጽ እኩል ሲሆን ሊቀመንበሩ ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፣
7. የበጎ አድራጎት የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት በማናቸውም ጊዜ ቢሆን የዲሞክራሲ መርሆችን የተከተለ መሆን አለበት፣
8. የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት እራሳቸውን ለቦርድ ምርጫ በዕጩነት ማቅረብ አይችሉም፡፡ሆኖም ግን ቦርዱ ካመነበት ከአስመራጭ ኮሚቴነት በማንሳት በእጩነት ሊያቀርባቸው ይችላል፣
9. አስመራጭ ኮሚቴው በስራላይ ያሉ የቦርድ አባላት የስራ ዘመን ከማብቃቱ ከ30 የስራ ቀናት በፊት ተተኪ የቦርድ አባላትን ማስመረጥ እና ማዘጋጀት አለበት፡፡

10.በንዑስ አንቀጽ 9 የተጠቀሰው እንዳለ ሆኖአዲሶቹ ተመራጮች የነባር የቦርድ አባላት የስራ ዘመን ባለቀ 30 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ አስመራጭ ኮሚቴው ስራቸውን ተረክበው እንዲሰሩ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፣

11. የቀድሞ ተመራጮች በምርጫ ከተሰናበቱ ዕለት ጀምሮ ከቦርዱ ውሣኔ ውጪ ከርክክብ በስተቀር ስራውን ማንቀሳቀስ አይችሉም፣

12. በቦርዱ ጉባኤ አጀንዳ ላይ ቀርበው ያልጸደቁና ያልሰፈሩ ጉዳዮችን በተመለከተ የተሰጡ ውሣኔዎች ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፣

አንቀጽ 18፡<u>የቦርድ አባላት የስራ ዘመን</u>

1. የቦርድ ሰብሳቢ ምክትል ሰብሳቢ እና ፀሐፊ የስራ ዘመን ሶስት ዓመት ይሆናል፡፡ ነገር ግን የተቀሩት የቦርድ አባላት የሥራ ዘመን አራት ዓመት ይሆናል፡፡
2. በንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው እንዳለ ሆኖ የቦርድ አባላት የስራ ዘመን በሚያበቃበት ወቅት አንቀፅ 17 ንዑስ አንቀፅ (5) መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል ፡፡

**አንቀጽ 19፡ <u>የድርጅ ሥራ አስኪያጅ ተግባርና ኃላፊነት</u>**

የበጎ አድራጎቱ ድርጅት ሥራ አስኪያጅ ተጠሪነቱ ለቦርድ ሆኖ የሚከተሉትን ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡፡

1. በማናቸውም አካል ዘንድ የበጎ አድራጐት ድርጅቱ ይወክላል፣ የበጎ አድራጐት ድርጅን ሥራ በተመለከተ ማናቸውም ጉዳዮች ይፈጽማል፣ ውክልና ይሰጣል፣ በበጎ አድራጐት ድርጅቱ ስም የደብዳቤ ልውውጦችን ያደርጋል ውል ይዋዋላል፣
2. የበጎ አድራጎት ስም የሚከፈተውን የባንክ ሂሣብ እና ቼክ ወይም ሐዋላ ከሂሣብ ሹሙ ጋር በጣምራ ፊርማ ያንቀሳቅሳል፣
3. በቦርድ የሚተላለፉ ውሣኔዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፣
4. በጎ አድራጎቱ የየሶስት ወር እና ዓመታዊ የሥራና የፋይናንስ ሪፖርቶች እያዘጋጀ (በየሶስት ወሩ እና በየዓመቱ) ለቦርዱ ያቀርባል፣
5. የበጎ አድራጐት ድርጅቱ ፖሊሲ በማውጣትና የበጀት እና የሥራ እቅድ በማዘጋጀት ለቦርዱ ያቀርባል፣
6. በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ለበጎ አድራጐት ድርጅቱ ገቢ የሚገኝበትን ዘዴ ይቀይሳል፣ የበጎ አድራጐት ድርጅቱ ዓላማ ከግብ ሊያደርሱ የሚችሉ ስልቶችን በመቀየስ ያስፈጽማል፣
7. ቦርዱ በሚያወጣው የአስተዳደር ደንብ መሠረት ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ያሰናብታል፣ ደመወዛቸውንና አበላቸውን ይወስናል፣

8. ከሂሣብ ሹሙ እና ከገንዘብ ያዡ የሥራ ኃላፊነቶች ውጭ ያሉትን የሥራ ድልድሎች በማዘጋጀት ለቦርዱ ያቀርባል፣
9. ሂሣብ ሹምና ገንዘብ ያዥን ጨምሮ፣ በስሩ የሚገኙትን ሠራተኞች እያስተባበረ፣ እየተከታተለና እየተቆጣጠረ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ የዕለት ተዕለት የሥራ እንቅስቃሴ ይመራል፣
10. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ የሥራ እንቅስቃሴ በተመለከተ ሌሎች የማኔጅመንት ውሣኔዎችን ይሰጣል፣
11. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ ወይም የቦርዱን ውሣኔን በማይቃረን ሁኔታ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**አንቀጽ 20፡ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ሂሣብ ሹም ተግባርና ኃላፊነት**

ሂሣብ ሹሙ ተጠሪነቱ ለበጎ አድራጎት ድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ሆኖ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፤

1. የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ገቢና ወጪ ሂሣብ ይቆጣጠራል፣ በትክክል እንዲመዘገብና እንዲያዝ ያደርጋል፣
2. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ሂሣብ የሚንቀሳቀሰው በታወቀ የሂሣብ አሠራር ደንብ መሠረት መሆኑን ይቆጣጠራል፣
3. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ የባንክ ሂሣብና ቼክ ወይም ሐዋላ ከሥራ አስኪያጁ ጋር በጣምራ ፊርማ ያንቀሳቅሳል፣
4. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ የሂሣብ መዛግብት እና የተለያዩ ሰነዶች በጥንቃቄ እንዲያዙ ያደርጋል፣
5. የሂሣብ መዝገብ፣ ገቢ እና ወጪ፣ ሀብት እና ዕዳን ያካተተ ሰነድ ያዘጋጃል፣
6. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ገቢ በሚያስገኙ ሥራዎች ላይ በሚሠማራበት ጊዜ ለዚሁ ሥራ የሚውሉ የተለያዩ የሂሣብ መዛግብት እንዲያዙ ያደርጋል፡፡

**አንቀጽ 21፡ የድርጅቱ ገንዘብ ያዥ ተግባርና ኃላፊነት**

ገንዘብ ያዡ ተጠሪነቱ ለበጎ አድራጎት ድርጅቱ ሂሳብ ሹም ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃፊነቶች ይኖሩታል፤

1. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ገቢዎች በህጋዊ ደረሰኝ ይሰበስባል፣
2. የተሰብሳቢውን ገንዘብ አገር ውስጥ በሚገኝ ባንክ ገቢ ያደርጋል፣ ገቢ ያደረገበትን ደረሰኝ በጥንቃቄ ያስቀምጣል፣

3. ለሥራ ማስኬጃና ለድርጅቱ ጥቃቅን ወጪዎች የሚሆን ከብር 10,000 (አስር ሺህ ብር) ያልበለጠ መጠባበቂያ ገንዘብ ይይዛል፣
4. ከሂሣብ ሹሙ ጋር የወጪና የገቢ ሂሣብ በየወሩ ያመሳክራል፣
5. የበጎ አድራጐት ድርጅቱን ቼክ ይይዛል፣
6. በጣምራ ፊርማ (በሂሣብ ሹሙ እና በሥራ አስኪያጁ) ሲታዘዝ ወጪ ያደርጋል።

አንቀጽ 22፡ <u>የኦዲተር ኃላፊነትና ተግባር</u>

1. የበጎ አድራጎት ኦዲተር ድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ወይም የቦርድ አባል ሊሆን አይችልም።
2. ኦዲተሩ ተጠሪነቱ ለቦርድ ሆኖ፤ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-
   - 2.1 የበጎ አድራጐት ድርጅቱ የገንዘብና የንብረት አስተዳደር ትክክለኛነት ይቆጣጠራል፣
   - 2.2 የበጎ አድራጐት ድርጅቱ የሥራ እንቅስቃሴ በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት መካሄዱን ያረጋግጣል፣
   - 2.3 በኢትዮጵያ ተቀባይነት ባገኙ መመዘኛዎች መሠረት ዓመታዊ የኦዲት ሪፖርት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል።

አንቀጽ 23፡ <u>የድርጅቱ የገቢ ምንጭ</u>

የበጎ አድራጎት የገቢ ምንጭ የአባላት መዋጮ፣በቦርድ ውሳኔ ከሕዝባዊ መዋጮ፣ ከገቢ ማስገኛ ስራዎችና ከእርዳታ ሰጪዎች የሚገኝ ገንዘብ ወይም ንብረት በገቢ ምንጭነት ሊወሰድ ይችላል።

አንቀጽ 24፡ <u>የበጎ አድራጎት</u> <u>መተዳደሪያ ደንብ ስለማሻሻል</u>

1. የዚህ መተዳደሪያ ደንብ የማሻሻያ ሀሳብ ከቦርድ አባላት ¼ኛ ባላነሱ አባላት ጠያቂነት በስብሰባ አጀንዳነት ይያዛል።
2. የዚህ መተዳደሪያ ደንብ የማሻሻያ ሀሳብ በቦርዱ መደበኛ ስብሰባ የሚወሰን ሆኖ የማሻሻያ ጥያቄው ለቦርድ ሰብሳቢ፣ም/ሰብሳቢ ወይም ጸሐፊ ጥሪ ከመሰራጨቱ በፊት መቅረብ ይኖርበታል።
3. የመተዳደሪያ ደንቡ የሚሻሻለው የማሻሻያ ሀሳቡ ከግማሽ በላይ አባላት በተገኙበት የቦርድ ስብሰባ ¾ኛ ድምጽ ሲያገኝ ነው።
4. የመተዳደሪያ ደንቡ እንዲሻሻል የተላለፈውን ውሳኔ ባለስልጣን መስርያቤቱ ያላጸደቀው እንደሆን ባልጸደቀበት ጉዳይ ላይ የሚወያይ ስብሰባ ይጠራል።

5. እንዲሻሻል የተወሰነው የመተዳደሪያ ደንብ በባለስልጣን መስርያቤቱ በኩል ታይቶ ከመጽደቁ በፊት ስራ ላይ ሊውል አይችልም፡፡

**አንቀጽ 25፡ <u>ስለበጎ አድራጎት ድርጅቱ መዋሃድና መለወጥ</u>**

1. በጎ አድራጎት ድርጅቱ ወደ ተለያዩ የበጎ አድራት ድርጅቶች የሚከፋፈለው፣ ከሌላ የበጎ አድራጎት ድርጅት ጋር የሚዋሃደው ወይም ወደ ሌላ አይነት በጎ አድራጎት ድርጅትነት የሚለወጠው በቦርዱ በ¾ኛ ድምፅ ሲወሰን ነው፡፡
2. የበጎ አድራጎት ጋር የሚዋሃደው በጎ አአድራጎት ድርጅት ጋር የሚደረገውን ድርድር የሚያከናውነው ኮሚቴ የቦርዱ ሰብሳቢ፣ምክትል ሰብሳቢ ፣ ፀሀፊ እና የድርጅቱን ሥራ አስኪያጅ ማካተት ይኖርበታል፡፡

**አንቀጽ 26፡ <u>የበጎ አድራጎት መፍረስ</u>**

1. በጎ አድራጎት ድርጅቱ የሚፈርሰው የቦርድ አባላት ድርጅቱ እንዲፈርስ በ¾ኛ ድምፅ ሲወስኑ ነው፡፡
2. የበጎ አድራጎት ወቅታዊ የስራ ክንንውን እና የሂሳብ መግለጫ ከማፍረስ ውሳኔው ጋር በማያያዝ ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን ያቀርባል፡፡
3. የበጎ አድራጎት ንብረቱን በቦርዱ ውሳኔ ተመሳሳይ አላማ ላላቸው ድርጅቶች አስተላልፎ የስተላለፊበትን መረጃ ባለስልጣን መስርያቤቱ ያቀርባል፡፡

**አንቀጽ 27፡<u>የመተዳደሪያ ደንብ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ የመተዳደሪያ ደንብ ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን ከጸደቀበት2015 ዓ. ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**<u>የመስራች አባላት ስምና ፊርማ</u>**

| ተ.ቁ | ስም | ፊርማ |
|---|---|---|
| 1 | ቻርለስ ኦካሪያ | [signature] |
| 2 | ውዴ ዘርጋ | [signature] |

## ኦሀናኤዜ ኢዲኢቦ ኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅት (OHANAEZE NDIGBO ETHIOPIA CHARITY ORGANIZATION)

### የመስራቾች ቃለ ጉባኤ

የስብሰባው ቀን፡ ግንቦት 21/2015

የስብሰባው ሰዓት፡ ከ 8:00 ሰዓት እስከ 9:30 ሰዓት

ስብሰባው የበቀው ሰዓት፡ 11:30 ሰዓት

የስብሰባው ቦታ፡ አዲስ አበባ

**በስብሰባው ላይ የተገኙት የመስራች አባላት ስም**

| ተ.ቁ | የመስራቾች ሙሉ ስም | ዜግነት | ከተማ | ክ/ከተማ | ወረዳ | ስልክ ቁጥር |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ቻርለስ ኦካሪያ | ናይጄሪያ | አዲስ አበባ | | | 0991578121 |
| 2 | ውዱ ዘርጋ ታደሰ | ኢትዮጵያዊ | አዲስ አበባ | ቦሌ | 01 | 0912142230 |

**የድርጅቱ አጀንዳዎች፡-**

1. የድርጅቱ ስያሜን መሰየም
2. ድርጅቱን ለመመስረት መነሻ የሆኑ ምክንያቶች
3. የድርጅቱ አላማ ማጽደቅ
4. የድርጅቱ የቦርድ አባላት መምረጥ እና የስራ ድርሻ መሰየም

**አጀንዳ 1 የድርጅቱ ስያሜን መሰየም**

ይህን ድርጅት ለማቋቋም የድርጅቱንም ስያሜ ለመሰየም ውይይት ካደረግን በኃላ ትክክለኛውን መጠርያ የተለያዩ ስሞችን ካወዳደርን በኃላ የምንሰራውንም ስራ ይገልፅልናል ያልነውን ኦሀናኤዜ ኢዲኢቦ ኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅት (OHANAEZE NDIJBO ETHIOPIA CHARITY ORGANIZATION) ስያሜ ለመጠቀም ወስነናል ።

**አጀንዳ 2 ድርጅቱን ለመመስረት መነሻ የሆኑ ምክንያቶች**

መንግስት ያልደረሰባቸውን የልማት ስራዎችን እንዲሁም ከመንግስት ጎን በመሆን ማህበረሰቡን ከልማቱ ተጠቃሚ እንዲሆን አቅማችን የቻለውን ለማህበረሰቡ ለመስራት እንዲሁም ሀገራችንን

የዜጎች የመደራጀት መብት ቀደም ሲል ከነበረው አዋጅ ተሻሽሎ አሁን ያለው ዕድል የተሻለ መሆኑ እንዲሁም የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን አዋጅ ያመቻቸውን የመደራጀት መብት ታሳቢ በማድረግ፡ ያለንን ክህሎት፣ እውቀት፣ ጉልበት እና ገንዘብ መጠቀም ለሀገርና ለህዝባችን አቅማችን በፈቀደ ሁሉ ለመስራት ይህን ድርጅት ለመመስረት ዋነኛ ምክንያቶች ሆኗል።

**አጀንዳ 3 የድርጅቱ አለማ ማጽደቅ**

ኦሀናኤዜ ኢዲኢቦ ኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅት (OHANAEZE NDIGBO ETHIOPIA CHARITY ORGANIZATION)

ዋና ዓላማ

- ለችግር የተጋለጡ የህብረተሰብ ክፍሎች ኢኮኖሚያዊ ድጋፍ ማድረግ፤
- በጤና ተቋማት ላይ የሚታዩ የህክምና ቁሳቁሶች ችሮችን ለመቅረፍ የተለያዩ ግብአቶችን ማቅረብ፤
- ዝቅተኛ ገቢ ላላቸዉና ረዳትና ደጋፊ ለሌቸዉ አረጋውያን በቁሳቁስ ድጋፍ ማድረግ፤
- የትምህርት እድል ያላገኙ ወጣቶችን የትምህርት እድል እንዲያገኙ ማድረግ

**አጀንዳ 4 የድርጅቱ የቦርድ አባላት መምረጥ እና የስራ ድርሽ መሰየም**

ኦሀናኤዜ ኢዲኢቦ ኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅት (OHANAEZE NDIGBO ETHIOPIA CHARITY ORGANIZATION) ድርጅት መስራቾች ከዚህ በላይ የመሰረቱትን ድርጅት የቦርድ አባላትን የመመረጥና የስራ ድርሻ የመሰየም ሁኔታን በተመለከተ ለድርጅቱ ሁለንተናዊ እድገትና የስራ ቅልጥፍና ብሎም የተለያየ ስትራቴጂካዊ ስልትን በመቀየስና ከፍተኛ አስተዳዳራዊ ስራዎችን ለመወጣት የሚችሉ የቦርድ አባላትን ባላቸዉ የትምህርት ደረጃ ባካበቱት ከፍተኛ ልምድ እና ተቀባይነት ያለዉን ማህበራዊ እሴቶቻቸዉን ታሳቢ በማድረግ የሚከተሉትን የድርጅቱ የቦርድ አባላት አድርጎ መርጧል።

- ፍራንሲስ ጆን ኦኬችኩ — የቦርድ ሰብሰቢ
- ዳንኤል ኡጉ — ም/ ሰብሳቢ
- ኤሞስ ኢኬዴቹኩ — ፀሀፊ
- ኦማሌቻ ኦኬቹኩ — አባል
- ኢፌቹኩ ኦኬቹኩ — አባል
- ሰላማዊት ወጋየሁ — አባል

የዜጎች የመደራጀት መብት ቀደም ሲል ከነበረው አዋጅ ተሻሽሎ አሁን ያለው ዕድል የተሻለ መሆኑ እንዲሁም የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን አዋጅ ያመቻቸውን የመደራጀት መብት ታሳቢ በማድረግ፡ ያለንን ክህሎት፣ እውቀት፣ ጉልበት እና ገንዘብ መጠቀም ለሀገርና ለህዝባችን አቅማችን በፈቀደ ሁሉ ለመስራት ይህን ድርጅት ለመመስረት ዋነኛ ምክንያቶች ሆኗል፡፡

<u>አጀንዳ 3 የድርጅቱ አለማ ማጽደቅ</u>

ኦሀናኤዜ ኢንዲኢቦ ኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅት (OHANAEZE NDIGBO ETHIOPIA CHARITY ORGANIZATION)

ዋና ዓላማ

- ለችግር የተጋለጡ የህብረተሰብ ክፍሎች ኢኮኖሚያዊ ድጋፍ ማድረግ፤
- በጤና ተቋማት ላይ የሚታዩ የህክምና ቁሳቁሶች ችሮችን ለመቅረፍ የተለያዩ ግብአቶችን ማቅረብ፤
- ዝቅተኛ ገቢ ላላቸዉና ረዳትና ደጋፊ ለሌቸዉ አረጋውያን በቁሳቁስ ድጋፍ ማድረግ፤
- የትምህርት እድል ያላገኙ ወጣቶችን የትምህርት እድል እንዲያገኙ ማድረግ

<u>አጀንዳ 4 የድርጅቱ የቦርድ አባላት መምረጥ እና የስራ ድርሽ መሰየም</u>

ኦሀናኤዜ ኢንዲኢቦ ኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅት (OHANAEZE NDIGBO ETHIOPIA CHARITY ORGANIZATION) ድርጅት መስራቾች ከዚህ በላይ የመሰረቱትን ድርጅት የቦርድ አባላትን የመመረጥና የስራ ድርሻ የመሰየም ሁኔታን በተመለከተ <u>ለድርጅቱ ሁለንተናዊ እድገትና የስራ ቅልጥፍና ብሎም የተለያየ ስትራቴጂካዊ ስልትን በመቀየስና ከፍተኛ አስተዳዳራዊ ስራዎችን ለመወጣት የሚችሉ የቦርድ አባላትን ባላቸዉ የትምህርት ደረጃ ባካበቱት ከፍተኛ ልምድ እና ተቀባይነት ያለዉን ማህበራዊ እሴቶቻቸዉን ታሳቢ በማድረግ የሚከተሉትን የድርጅቱ የቦርድ አባላት አድርጎ መርጧል፡፡</u>

- ፍራንሲስ ጆን ኦኬችኩ — የቦርድ ሰብሰቢ
- ዳንኤል ኡጉ — ም/ ሰብሳቢ
- ኤሞስ ኢኬዴቹኩ — ፀሀፊ
- ኦማሌቻ ኦኬቹኩ — አባል
- ኢፊቹኩ ኦኬቹኩ — አባል
- ሰላማዊት ወጋየሁ — አባል